የኢትዮጵያ ፪ሺ ምዕተ ዓመት ዝግጅት

JULY 23, 2007

## ከኢትዮጵያ ሚሊኒየም አዘጋጅ ኮሚቴ በሎስ አንጀለስ የተሰጠ መግለጫ::

በጥቂት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውን አነሳሽነት የሚሊኒየም አዘጋጅ ኮሚቴ ከተቋቋመ ቆይቷል:: ኮሚቴው ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በየሳምንቱ እየተገናኘ በዓሉን ለማክበር የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ለሟሟላት ውይይትና ጥረት በማድረግ ሂደት ላይ ይገኛል::

የኮሚቴው አባሎች የማንኛውንም የፖለቲካ ድርጅት ወይም ሃይማኖት በመወከል የተጠናቀሩ አይደሉም:: የኮሚቴዉም አላማ በሺህ ዓመት አንድ ግዜ ብቻ የሚውለውን ሚሊኒየም በሎሰ አንጀለስና አካባቢዋ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በአንድነትና በጋራ እነዲያከበሩ ለመርዳትና ለማዘጋጀት ብቻ ነው:: እንደዚሁም ደግሞ በዚሁ አጋጣሚ ያገራችንን ጥንታዊ ታሪክና፤እየደረሰባት ያለውን ችግር፤ ውጥረት ለመላው ዓለም ለማሰማትና ለማስጋባትም ጭምር ነው::

ኮሚቴው በዚህ ዓላማና መንፈስ ተገፋፍቶ የጀመረው ጥረት አንዳንድ ችግሮችና እንቅፋቶች አጋጥመውት ነበር:: በሊትል ኢትዮጵያ (Little Ethiopia) የሚገኙ ጥቂት ኢትዮጵያን የንግድ ባለቤቶች ዓመታዊ በዓል (Little Ethiopia Street Festival) በሚሊነየም ወቅትና አካባቢ ለማክበር አቅደው ሲንቀሳቀሱ እንደነበር የሚታውቅና የሚታወስ ነው::

በመሆኑም የማህበረ ሰቡ አባሎችና የሀይማኖት አባቶች በታዛቢነትና ባማካሪነት በተገኙበት ስብሰባ ላይ የተፈጠረውን ችግር በተደጋጋሚ ከተወያዩ በኃላ ወደ አንድ አስታራቂ ስምምነት ደርሰዋል::

የንግዱ ባለንብረቶችም የሊትል ኢትዮጵያን ዓመታዊ በዓል (Little Ethiopia Street Festival) ከሚሊኒየሙ ክብረ በዓል በኃላ እንደአስፈላጊነቱ ወደፊት እንዲወሰን ተስማምተዋል::

የሊትል ኢትዮጵያ የንግድ ባለንብረቶች በሙሉ ሚሊኒየሙን ለማክበር ከኮሚቴው ጋር እንደሚተባበሩ ተገልጧል:: ሁላችንም ሚሊኒየሙን በአንድነት እናከብራለን ማለት ነው::

የንግዱን ክፍል የሚወክሉ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ከጠቅላላው የአካባቢው ማህበረሰብ ገር ሆነው ሚሊኒየሙን ለማክበር በመሰማማታቸው እጅግ ተደስተናል በማሕበረ ሰቡ ስም የሚሊኒየም አዘጋጅ ኮሚቴው ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል::

በበጎ ፈቃደኝነትና በራሳቸው አነሳሽነት ለስምምነቱ የምክርና የሐሳአብ አስተዋፅኦ ላደረጉልን ሁሉ ከፍ ያለ መስጋናችንን እናቀርባለን::ይሁን አንጂ የበዓሉን አከባበር የተሟላ ለማድረግ የገንዘብና የጉልበት እርዳታ ያስፈልገዋል::

የሁለት ሺህ ዓመት ሰው ይበለን !!!
እንረዳዳ/በሰላም ያድርሰን !!!

ስለ ሚሊኒየም ዝግጅት ለማወቅና ለመረዳት የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ሬዲዮ ሰምንታዊ ዝግጅት የሳምንቱ እሁድ From 4 pm to 4:30 pm 900 AM KALI እንዲሁም ድኅረገፃችንን ለመጎብኘት ለምትፈልጉ www.ethioy2kla.org መሆኑን ሰንገልፅ በደስታ ነው::